## Case Comment

## የፍቺ ውሳኔ የጋብቻ ውልን ቀሪ ያደርጋል ወይስ አያደርግም?

**በዶ/ር ደጀኔ ግርማ ጃንካ**

**በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የህግ መምህር**

**ጠበቃና የህግ አማካሪ**

በኢትዮጵያ ውስጥ አሁን ባለው ሁኔታ ህጋዊ ጋብቻ ሁለት ተቃራኒ ፆታ ባላቸው ሰዎች መካከል ሊፈፀም የሚችል ግንኙነት ወይም ድርጊት መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡[1] ይህ ግኙነት በፅሁፍ ውል መመስረት ያለበት እና በአራት ምስክሮች ማለትም ሁለት ከባል እና ሁለት ከሚስት በኩል መረጋገጥ ያለበት ውል እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡[2] በዚህ ውል መሰረት ተጋቢዎች የጋብቻ/የትዳር ግንኙነት በመካከላቸው ሲመሰርቱ ቀሪውን የህይወት ዘመናቸውን አብሮ በፍቅር፣ በመከባበር፣ መተጋጋዝ፣ እና በመረዳዳት ለማሳለለፍ በመወሰን ነው፡፡[3] በዚሁ መሰረት ሰዎች ወደ ጋብቻ ይጋባሉ፤ ትዳር ይመሰርታሉ፣ ከትዳር አጋሮቻቸው ጋር እስከ መጨረሻም ይኖራሉ፡፡ ነገር ግን በተለየዩ ምክንያቶች የታሰበው ሳይሆን ወደ ጋብቻ ከሚገቡ ሰዎች መካክ የተወሰኑቱ ጋብቻቸው ሊፈርስ ይችላል፡፡ ከእነዚህ ምክንያቶች መካከከል አንዱ ፍቺ ነው፡፡ ፍቺ በፍርድ ቤት የሚሰጥ ውሳኔ ሲሆን ይህ ውሳኔ በተጋቢዎች መካከል የነበረው ግንኙነት የሚያቋርጥ ነው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በርካታ ነጥቦች ሊነሱ ቢችሉም የዚህ ፅሁፍ ትኩረት አንዱ ላይ ብቻ ሲሆን እርሱም *ሰዎች የፅሁፍ የጋብቻ ውል ፈፅም ከተጋቡ በኋላ ጋብቻቸው በፍ/ቤት ቢፈርስ የፍቺ ውሳኔ በጋብቻ ውል ላይ ያለው ውጤት ምንድን ነው?* የሚል ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ መንስዔ የሆነ አንድ የፍ/ቤት ውሳኔ ሲሆን የነገሩ አመጣጥ በአጭሩ እንደሚከተለው ነው፡፡

ከሳሽ አቶ “ሀ” በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የካ ምድብ ፍ/ብሄር ችሎት በኮ/መ/ቁ 128733 በተከሳሽ ወ/ሮ “ለ” ላይ በ19/11/2009 ዓ.ም የውል ይፍረስ ክስ ያቀረበ ሲሆን ክሱም “እኔና ተከሳሽ በ07/06/2007 ዓ.ም. ለመጋባት የፈረምነው የጋብቻ ውል የተፈረመው በተከሳሽ ተንኮልና ማታለል ስለሆነ ይህ የጋብቻ ውል ይፍረስልኝ፣ ህጋዊ ውጤት የለውም ይባልልኝ” የሚል ነው፡፡[4] ተከሳሽ ወ/ሮ “ለ” በበኩላቸው የቀረበባቸውን ክስ የተቃወሙት ሲሆን መቃወሚያውም “እኔ እና ተከሳሽ ተዋድደን እና ተፋቃቅረን ያለአንዳች ጫና የሃገር ሽማግሎዎችና የሃይማኖት አባቶች ባሉበት ቦታ በ07/06/2007 ዓ.ም. ትዳር ለመመስረት የጋብቻ ውል የፈረምን ቢሆንም በመካከላቸው በተፈጠረው ችግር ምክንያት ይህ ውል ፈርሶ ጋብቻችን ቀሪ እንዲሆን በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት 5ኛ ፍ/ብሄር ችሎት በመ/ቁ 122235 በቀን በ22/07/2009 ዓ.ም. ተወስነዋል፤ በአንድ ችሎት የፈረሰ ውል ደግሞ እንደገና በሌላ ችሎት እንዲፈርስ ጥያቄ ሊነሳበት ስለማይችል ወይም አንድ ጊዜ የፈረሰ ውል እንደገና ይፍረስ የሚል ክስ ሊቀርብ ስለማይችል አሁን የቀረበብኝ ክስ የክስ ምክንያት (cause of action) የለውም ተብሎ በፍ/ስ/ስ/ህግ አንቀፅ 33(2) መሰረት ውድቅ መደረግ አለበት” የሚል ነበር፡፡[5]

---

[1]ተመሳሳይ ፆታ ያላቸው ሰዎች እንዲህ ዓይነት ግንኙነት ሊፈጥ አይችሉም፤ ምክንያቱም በወንጀል ህጉ አንቀፅ 629 መሰረት የተከለከለ ነው፡፡

[2]ለምሳሌ የተሸሻለውን የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 44ን እና የኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 60ን ይመልከቱ፡፡

[3]የተሸሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 49 ባል እና ሚስት አርስ በእርሳቸው መከባበር፣ መተጋጋዝ፣ እና መረዳዳት እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ የኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 65(2) ተመሳሳይ ድንጋጌ ይዘዋል፡፡

[4]የክሱን ሙሉ መረጃ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የካ ምድብ ፍ/ብሄር ችሎት ከኮ/መ/ቁ 128733 መመልከት ይቻላል፡፡

[5]የመልሱን ሙሉ መረጃ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የካ ምድብ 5ኛ ፍ/ብሄር ችሎት በመ/ቁ 122235 መመልከት ይቻላል፡፡ ይህ ጉዳይ ተከሳሽ ባቀረቡት መቃወሚያ መሰረት ባይሆንም እስከ ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ሄዶ የከሳሽ ክስ ውድቅ ተደርጓል፤ በዚህ ምክንያት ተከራካሪዎች ወገኖች በመጨረሻ ላይ ባደረጉት ስምምነት መሰረት የንብረት ክፍፍል ተፈፅዋል፡፡

ይህ አጭር ፅሁፍ ለመዳሰስ ከሚያስበው ነጥብ አንፃር የነበረው ታሪክ ከላይ የተጠቀሰው ሲሆን ክስ የቀረበለት ችሎት ከላይ የተገለፀውን የተከሳሽ መቃወሚያ አልፎታል ወይም ውድቅ አድርጎታል፡፡ ይህ መቃወሚያ ውድቅ የተደረገው እንደ አዲስ ይፍረስ ተብሎ ክስ የቀረበበት ውል ቀድሞውኑ በሌላ ችሎት ለፍቺ ጥያቄ መሰረት ሆኖ ክስ ቀርቦበት ጉዳዩን የያዘው የቤተሰብ ችሎት ውሉን አፍርሶ ጋብቻው በፍቺ ቀሪ እንዲሆን እንደወሰነ እየታወቀ ነበር፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አካሄድ *በውል መሰረት የተፈፀመ ጋብቻ ቀሪ እንዲሆን የፍቺ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ውሉ ለብቻው ፀንቶ የሚቆይበነት አግባብ አለ ወይ?* የሚል ጥያቄ የሚያስነሳ ይሆናል፡፡ የፍቺ ውሳኔ ሰዎች ትዳር የመሰረቱበትን ቃል-ኪዳን (ውል) መፍረስ የማያስከትል ከሆነ እንዴት ግንኙነት ሊያቋርጥ ይችላል? ተጋቢዎቹን አንድ ላይ አስሮ ባል እና ሚስት ያደረጋቸው ውሉ አይደለም ወይ? ተጋቢዎቹ በፍ/ቤት ውሳኔ መሰረት ተለያዩ ማለት አንድ ላይ ያስተሳሰራቸው ወል (ህግ)[6] ቀሪ ሆነ (ተሻረ) ማለት አይደለም ወይ? ውሉ ፍቺ በሚወሰንበት ጊዜ ቀሪ ከሆነ ደግሞ በሌላ ችሎት ውሉ ይፍረስልኝ የሚል ጥያቄ ሊቀርብ ይችላል ወይ? እነዚህ ጥያቄዎች መልስ የሚፈልጉ ናቸው፡፡ በመጀመሪያ እይታ ቀላል ሊመስሉ የሚችሉ ነገር ግን በተግባር ከፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እስከ ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ የደረሰ ክርክርን ያስከተሉ ነበሩ፡፡

ተጋቢዎች ሁለት ዓይነት ውሎችን ሊፈፅሙ የሚችሉ ሲሆን ውሎቹም ጋብቻ የሚያቋቁሙበት ውል (የጋብቻ ውል) እና የንብረት ግንኙነቶቻቸውን የሚቆጣጠሩበት ውል ናቸው፡፡ ከላይ የተገለፀው እና ከሳሽ እንዲፈርስለት የጠየቀው ውል በከሳሽ እና በተከሳሽ መካከል የሚኖረውን የንብረት ግንኙነት ለመቆጣጠር የተፈፀመ ራሱን የተለየ ውል አይደለም፡፡ ከሳሽ እንዲፈርስለት የጠየቀው ውል ጋብቻው እራሱ የተመሰረተበት ውል ነው፡፡ በመሆኑን በሁለቱ ወገኖች መካከል የነበረው ውል አንድ ብቻ ነበር፡፡ የፍቺ ውሳኔ እንዲሰጥ ከሳሽ ጥያቄ አቅርቦ የነበረው ከሳሽ እራሱ ሲሆን የፍቺ ማመልከቻውን ለፍ/ቤት ሲያቀርብ ይሄንኑ ውል እንደ ማስረጃ በማያያዝ ነበር፤ የፍቺ ውሳኔውም በዚሁ ውል መሰረት በሁለቱ ወገኖች መካከል የትዳር ግንኙነት የነበረ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ የተሰጠ ነበር፡፡

የሆነው ሆኖ ትዳር (ጋብቻ) የተመሰረተው በውሉ መሰረት እስከሆነ ድረስ ጋብቻው ቀሪ ሊሆን የሚችለው ሰዎቹን ያስተሳሰረው ቃል-ኪዳን ወይም ውል ቀሪ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ ውሉ ቀሪ ካልሆነ በውሉ መሰረት የተመሰረተው ግንኙነት ቀሪ ሊሆን አይችልም፤ ሁለቱ የአንድ ሳንቱም ሁለት ገፅታዎች ናቸው፡፡ በተጨማሪ የጋብቻ ውል ቀሪ የሚሆነው (ውጤት ማመንጨት የሚያቆመው) በውሉ ውስጥ የተካተቱ ሁሉንም ጉዳዮች በሚመለከት ነው እንጂ በከፍል የተጋቢዎችን የግል ግንኙነት በሚመለከት ብቻ ሊሆን አይችልም፡፡ በፍቺ ውሳኔ መሰረት ቀሪ የሆነ ውል በተጋቢዎች መካከል ያለውን የባልና የሚስት ሁኔታን ብቻ ቀሪ አድርጎ ሌሎች ጎዳዮችን በሚመለከት ፀንቶ ሊቀጥል አይችልም፡፡ የፍቺ ውሳኔ የጋብቻውን ውሉ እስከነሙሉ ይዘቱ ቀሪ የሚያደርግ ነው እንጂ የተጋቢዎችን የግል ግንኙነት በማቋረጥ ላይ ብቻ የሚገደብ አይደለም፡፡

ከላይ ከተሰጠው ማብራሪያ አንፃሪ ሲታይ በፍቺ ውሳኔ መሰረት ቀሪ የሆነ ውል እንዳልፈረሰ ተቆጥሮ ውሉ ይፍረስ የሚል አዲስ ክስ እንደገና የሚቀርብበት አግባብ አይኖርም፡፡ እንዲህ ዓይነት ክስ የሚቀርብ ከሆነ ክሱ መንስዔ ወይም የክስ ምክንያት (cause of action) ስለማይኖረው በፍ/ስ/ስ/ህግ አንቀፅ 33(2) መሰረት መቃወሚያ ከቀረበበት መቃወሚያው ተቀባይነት ሊኖረው ይገባል፡፡ ስለዚህ ከላይ በተጠቀሰው ጉዳይ ውስጥ በተከሳሽ በኩል በፍ/ስ/ስ/ህግ አንቀፅ 33(2) መሰረት ቀርቦ የነበረው መቃወሚያ ጉዳዩን በያዘው ፍ/ቤት ተቀባይነት አለማግኘቱ ስህተት ነበር፡፡[7] በእርግጥ በዚህ መቃወሚያ መሰረት ባይሆንም ጉዳዩ እስከ ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ደርሶ ተከሳሽ አሻናፊ ሊሆኑ ችሏል፡፡

---

[6] በፍ/ብሄር ህግ አንቀጽ 1731 መሰረት ውል በተዋዋይ ወገኖች መካከል ህግ ስለሆነ የጋብቻ ወል በተጋቢዎች መካከል ህግ ነው ማለት ይቻላል፡፡ የፍ/ብሄር ህግ አንቀጽ 1731(1) እና 1677(1) ይመልከቱ፡፡

[7]ከሳሽ በማንኛውም መንገድ ጉዳት ደረሰብኝ የሚል ከሆነ በሌላ መንገድ ካሳ መጠየቅ ይችል ይሆናል እንጂ የፈረሰን ውል እንዳልፈረሰ ቆጥሮ አዲስ የውል ይፍረስ ክስ ማቅረቡ ትክክል አይሆንም፤ አልነበረም፡፡